

## የFAMIS Select ማረጋገጫ ዝርዝር

- ልጆችዎ ለFAMIS ብቁ መሆናቸውን ያረጋግጡ።
- ለFAMIS በ**1-833-5CALLVA (833-522-5582)** በመደወል ወይም በመስመር ላይ በ**commonhelp. virginia.gov** ወይም በአካባቢዎ የማህበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ በመጎብኘት ያመልክቱ።
- በግል ወይም በአሰሪ ገንዘብ የተደገፈ የጤና መድህን ዕቅድ ለልጅዎ መሸፈን ይችል እንደሆነ ይመልከቱ።
- በጤና መድህን ዕቅድ የሚሸፈኑ አገልግሎቶችን በFAMIS ስር ከተካተቱት አገልግሎቶች ጋር ያወዳድሩ።
- እርስዎ የመረጡት የግል ወይም የአሰሪ የጤና ዕቅድ ወጪዎችን ይረዱ። ያስታውሱ፣ በFAMIS *Select* አማካኝነት በወር ለአንድ ልጅ $100 ከማግኘት እስከ ሙሉ የቤተሰብዎ ፕሪሚየም መጠን ድረስ ያገኛሉ። ሆኖም፣ አሁንም ፕሪሚየሙን፣ የድርሻ ክፍያዎችን፣ ተቀናሾችን እና ሌሎች ወጪዎችን ይከፍላሉ። FAMIS የወጪ መጋራት የለውም።
- FAMIS እና/ወይም የግል/የአሰሪ ዕቅድ መቀበላቸውን ለማየት ከልጅዎ ዶክተሮች ጋር ይነጋገሩ። አንዱን ሊወስዱ ይችላሉ ነገር ግን ሌላውን አይወስዱም።
- ወደ FAMIS መልሰው መቀየር ሚፈልጉበት ጊዜ በግል ወይም በአሰሪው ገንዘብ የሚደገፍ የጤና ዕቅድ መቼ እና እንዴት ማቋረጥ እንደሚችሉ ይመልከቱ እና ይረዱ።
- ለቤተሰብዎ የሚስማማውን ዕቅድ ይምረጡ።
- የFAMIS *Select* ርዳታ ማግኘቱን ለመቀጠል የFAMIS ሽፋንን በየዓመቱ ያድሱ።

## የማመለክተው እንዴት ነው?

ለFAMIS *Select* ፕሮግራም ለማመልከት በሚከተለው ነጻ ስልክ ይደውሉ፡-
**1-888-802-KIDS** (1-888-802-5437)

ያስታውሱ!
**መጀመሪያ በFAMIS ውስጥ መመዝገብ አለብዎት**

ለFAMIS ለማመልከት በመስመር ላይ ወደሚከተለው ይሂዱ
**commonhelp.virginia.gov**
ወይም በሚከተለው ነጻ ስልክ ይደውሉ፡-
**1-833-5CALLVA (833-522-5582)**
*Se habla español*
ወይም
የአካባቢዎን የማህበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ ይጎብኙ

ስለFAMIS እና በFAMIS ስለሚሸፈኑ አገልግሎቶች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ወደ **coverva.dmas.virginia.go** ይሂዱ

ይህንን ሰነድ በሌላ ቋንቋ በትልቅ ህትመት ወይም ለእርስዎ በሚመች ሌላ መንገድ ማግኘት ይችላሉ። ለCover Virginia በ 1-833-5CALLVA (TTY: 1-888-221-1590) ይደውሉ።

ይህ ተቋም በፕሮግራሞቹና አገልግሎቶቹ ውስጥ ዘርን፣ ቀለምን፣ ብሔራዊ ማንነትን፣ ጾታን፣ ዕድሜን ወይም አካል ጉዳተኝነትን መነሻ አድርጎ አድሎ አይሰራም።

FAMIS Select *የቨርጂኒያ ኮመንዌልዝ ፕሮግራም ነው*

***FAMIS 5 RVSD 0923***



FAMIS *Select*
**የፕሪሚየም ክፍያ እርዳታ ለFAMIS ቤተሰቦች**

# ለወላጆች የመምረጥ ስልጣን መስጠት!

## የFAMIS Select ምንድነው?

FAMIS *Select* በFAMIS ውስጥ ተመዘገቡ ልጆች ያሏቸው ወላጆች ከFAMIS የጤና መድህን ዕቅድ ወይም ከግል/ከአሰሪ ዕቅድ መካከል እንዲመርጡ ያስችላቸዋል። የግል/የአሰሪ ዕቅዶች ለመረጡ አብዛኛዎቹ ቤተሰቦች ለአንድ ልጅ የ100 ዶላር/በወር የፕሪሚየም እርዳታ ክፍያ ይሰጣል።

## ለFAMIS Select ብቁ የሆነው ማነው?

ለFAMIS *Select* ብቁ ለመሆን አንድ ልጅ የግል/የአሰሪ ዕቅድ ማግኘት እና ለFAMIS መጽደቅ አለበት። ማመልከቻ በሚያስገቡበት ጊዜ ልጅ ሌላ የጤና ሽፋን ሊኖረው አይገባም እና በፍርድ ቤት የታዘዘ የፖሊሲ ባለቤት ዕቅድ መሸፈን አይችልም።

## ጥቅማጥቅሞቹ ምንድን ናቸው?

FAMIS *Select* ልጅዎ ልዩ የጤና እንክብካቤ አቅራቢን እንዲያይ/እንድታይ ሊፈቅድለት/ሊፈቀድላት ይችላል። አንዳንድ ጊዜ አንድ ልጅ FAMIS የማይወስድ ዶክተር ወይም የጥርስ ሀኪም ማግኘቱን/ማግኘቷን እንዲቀጥል/እንድትቀጥል የግል ወይም የአሰሪ ዕቅድ በአውታረ መረባቸው ውስጥ ያሉትን የተለያዩ የአካባቢ አገልግሎት አቅራቢዎችን ሊያቀርብ ይችላል። ለአንዳንድ ቤተሰቦች የFAMIS *Select* ፕሪሚየም ዕርዳታ ክፍያ ለመላው ቤተሰብ የጤና ሽፋን በተመጣጣኝ ዋጋ የሚገኝ ለማድረግ በቂ ይሆናል።

ያስታውሱ፣ በFAMIS *Select* ውስጥ ያሉ ልጆች ወላጆቻቸው በሚመርጡት የግል የጤና ዕቅድ የጤና ጥቅማጥቅሞችን ያገኛሉ። የጤና ዕቅዶችን ማወዳደር እና ለቤተሰብዎ ከሁሉም የተሻለውን ዕቅድ መምረጥ አስፈላጊ ነው።

FAMIS የሚከተሉትን ይሸፍናል፡-

- የዶክተር ጉብኝቶች
- የሆስፒታል እና የድንገተኛ አደጋ እንክብካቤ
- የልጅ የጤና ክትትሎች
- የአይን እና የጥርስ እንክብካቤ
- የመድሃኒት ማዘዣዎች
- መርፌዎች
- የአዕምሮ ጤና ክብካቤ
- እና ሌሎች...



## ወጪዎቹ ምን ይሆናሉ?

FAMIS *Select* ወላጆች ለግል ወይም ለአሰሪ የጤና እቅዳቸው፣ ማናቸውንም ተቀናሾች ወይም የድርሻ ክፍያዎችን ጨምሮ እንዲከፍሉ ይጠይቃሉ። በምትኩ ለአንድ ልጅ በወር $100 የፕሪሚየም የእርዳታ ክፍያ ከFAMIS *Select* እስከ ጠቅላላ የቤተሰብ ፕሪሚየም ወጪ ድረስ ይቀበላሉ።

**ምሳሌ፡- በFAMIS *Select* ላይ 3 ልጆች ያሉት ቤተሰብ**

| | |
|---|---|
| የጤና ዕቅድ የቤተሰብ ፕሪሚየም በወር | $350 |
| የFAMIS *Select* የፕሪሚየም እርዳታ ክፍያ በወር | $300 |
| ጠቅላላ ወጪ ለቤተሰብ በወር | $50<br>+ ማናኛውም የድርሻ ክፍያዎች፣ የጋራ መድህን (coinsurance) እና ተቀናሾች |

## ልጄ ለምን ያህል ጊዜ ይመዘገባል/ትመዘገባለች?

አንድ ልጅ አሁንም ለFAMIS ብቁ እስከሆነ/እስከሆነች እና በግል ወይም በአሰሪ የገንዘብ ድጋፍ የጤና እቅድ ውስጥ እስከተመዘገበ/እስከተመዘገበች ድረስ ልጁ/ልጅቷ በFAMIS *Select* ውስጥ ይቆያል/ትቆያለች። የልጅ FAMIS ሽፋን በየዓመቱ መታደስ አለበት። ዕድሳት ካልተጠናቀቀ ልጁ/ልጅቷ የFAMIS ብቁነትን ያጣል/ታጣለች እና በ FAMIS *Select* ውስጥ መመዝገብ አይችልም/አትችልም።

በማንኛውም ጊዜ ልጅ በFAMIS ውስጥ ባለው የአስራ ሁለት ወራት የሽፋን ጊዜ፣ ወላጅ ልጃቸውን በFAMIS *Select* ውስጥ ማስመዝገብ ወይም ከFAMIS *Select* ማቋረጥ እና ወደ FAMIS መመለስ ይችላሉ። የልጁ/ልጅቷ ዓመታዊ የFAMIS እድሳት ጊዜ እስኪደርስ ድረስ ምንም ተጨማሪ የFAMIS ማመልከቻ አያስፈልግም።

## ለቤተሰቤ፣ ለFAMIS ወይም ለFAMIS Select ትክክለኛ ፕሮግራም የትኛው ነው?

በFAMIS ውስጥ ልጁ/ልጅቷ በFAMIS እና በFAMIS የአቅራቢዎች አውታረመረብ በኩል የጤና ጥቅማጥቅሞችን ያገኛል/ታገኛለች። ሁሉም በFAMIS የሚሸፈኑ አገልግሎቶች ይገኛሉ። የተሸፈኑ አገልግሎቶችን ዝርዝር ለማግኘት coverva.dmas.virginia.gov ይጎብኙ።

- ወላጆች **ምንም** ወርሃዊ ፕሪሚየሞችንን አይከፍሉም።
- በFAMIS ለሚሸፈኑ አገልግሎቶች ምንም አይነት የድርሻ ክፍያዎች የለም።
- የሚሸፈንላቸው ዕድሜያቸው ከ19 ዓመት በታች የሆኑ ብቁ ልጆች ብቻ ናቸው።

በFAMIS *Select* ውስጥ ልጁ/ልጅቷ ለFAMIS ብቁ መሆን አለበት/አለባት፣ እንዲሁም በግል ወይም በአሰሪ የጤና መድህን ዕቅድ ውስጥ ለመመዝገብ ብቁ መሆን አለበት/አለባት። ልጁ/ጇ በግል የጤና ዕቅድ አቅራቢዎች በኩል የጤና ጥቅማጥቅሞችን ያገኛል/ታገኛለች። በግል ወይም በአሰሪ ዕቅድ ስር የሚሸፈኑ አገልግሎቶች ብቻ ይገኛሉ።

- የእርስዎ የግል ዕቅድ የማይሸፍን ከሆነ FAMIS *Select* ክትባቶችን ይሸፍናል።
- ወላጆች ለግል ወይም ለአሰሪ ዕቅድ ወርሃዊ ፕሪሚየም ይከፍላሉ፣ ነገር ግን በወር 100 ዶላር ለአንድ ልጅ እስከ ጠቅላላ የቤተሰብ ፕሪሚየም ወጪ ይመለስላቸዋል።
- ወላጆች በግል ወይም በአሰሪ የጤና መድህን እቅድ የተቀመጠውን ማንኛውንም የተቀናሽ፣ የጋራ ክፍያ ወይም የጋራ መድህን መጠኖችን ከፍላሉ።
- አንዳንድ ጊዜ ቤተሰቦች ለመላው ቤተሰብ መድህን መክፈል እንዲችሉ ለመርዳት የFAMIS *Select* ፕሪሚየም እርዳታ ክፍያ በቂ ሊሆን ይችላል።

